የሰ/መ/ቁ. 61480

ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- አቶ ገ/እግዚአብሔር ከበደው - ጠበቃ አንተነህ ተካልኝ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ት ሠላማዊት ወ/ገብርኤል - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመቀሌ ቀዳማዊ ወያኔ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ መሰረትም ሟች እናታቸው ወ/ሮ ድንቅነሽ ድምጹ ከአመልካች ጋር በባልና ሚስትነት ሲኖሩ በጋራ ያፈሯቸው የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ጠቅላላ ድምሩ ብር 426,900.00 (አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር) ከሆነው የእናታቸውን ድርሻ ግማሽ ብር 213,450.00 (ሁለት መቶ አስራ ሶስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር) እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካችም ጉዳዩ በፍርድ ቀድሞ ማለቁንና በድጋሚ ዳኝነት የማይጠይቅበት መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስተው ከመከራከራቸው በተጨማሪ የዋና ጉዳይ ክርክርም አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ተጠሪ በክሱ የጠየቁትን ግማሽ ገንዘብ ከአራት ወንድሞቻቸው ጋር እንዲወስዱ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለመቐሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማጽናት የገንዘቡን መጠን ብቻ ወደ ብር 123,450.00 (አንድ መቶ ሃያ ሶስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር) ዝቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በጉዳዩ ላይ ሁለቱ የበታች ፍርድ ቤቶች የተለያየ ውሳኔ የሠጡበት በመሆኑ በይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ከሚቀርብ በስተቀር ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት መዝገቡ ተዘግቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት አይደለም

በማለት መዝገቡ የመዘጋቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ይህ ችሎትም በዚህ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙን በጽሑፍ እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ትእዛዝ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ክርክሩ የነበረው በሁለት በተመሳሳይ ክልል ኗሪ በሆኑ ግለሰቦች ሲሆን ክርክሩም የንብረት ግምት ክርክር መሆኑን፣ ክርክሩ የተጀመረው በወረዳ ፍርድ ቤት ሁኖ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ተገቢ ነው ያለውን ግምት እንዲከፍሉ ወስኖ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ይኸው ፍርድ ቤትም አመልካች ለክሱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑን እንዳለ በመቀበል የኃላፊነት መጠኑን ብቻ በማሻሻል መወሰኑን ነው፡፡ እንግዲህ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ሲቀርብለት የመጨረሻ ፍርድ አልተሰጠበትም በማለት መዝገቡን የዘጋው በሁለቱ የበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የተለያየ ነው በማለት ነው፡፡ እኛም የዚህኑ ትዕዛዝ ተገቢነት ተሻሽሎ ከወጣው የትግራይ ብሄራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 49/1994 አንቀፅ 16(ለ) ድንጋጌ አኳያ ተመልክተነዋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለባቸው የክልል ጉዳዮች የሰበር ስልጣን የሚኖረው በወረዳ ፍርድ ቤት ተወስነው በይግባኝ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም በጠቅላይ ፍርድ ቤት ያለቁ ጉዳዮች መሆናቸው ሲረጋገጥ መሆኑን ተጠቃሹ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ሁለት ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ተመሳሳይ ውሳኔ ከሰጡ ውሳኔው የመጨረሻ እንደሚሆንና በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን በአዋጁ አንቀጽ 17 መሰረት አዘጋጅቶ እንደሚያቀርብ ነው፡፡ በመሆኑም በክልሉ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 93/1997 አንቀፅ 30(2(ሀ)) ስር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሁኖ የበታች ፍርድ ቤቶች ተመሳሳይ ውሳኔ የሠጡበት ጉዳይ በድጋሚ ይግባኝ የሌለውና ሊቀርብ የሚችለው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ብቻ መሆኑን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ለመቅረብ ብቁ አይደለም በማለት መዝገቡን የዘጋው የበታች ፍርድ ቤቶች የተለያየ ውሳኔ በጉዳዩ ላይ ሰጥተዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካችን ኃላፊነትን በተመለከተ ሁለቱም ፍርድ ቤቶች ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ የወሰኑ ከመሆናቸውም በላይ ይግባኝ አቅራቢም የአሁኑ አመልካች የነበሩ በመሆኑና የይግባኝ መብት የተፈቀደው ከአንድ ጊዜ በላይ ስለመሆኑ የሚያመላክት የክልሉ የሕግ ማዕቀፍ በሌለበት ሁኔታ (ከይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት አንፃር) በጉዳዩ ላይ የተለያየ ውሳኔ ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበትና ሊታይ የሚችለውም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሁኖ እያለ መዝገቡ መዘጋቱ ከተሻሻለው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 49/1994 አንቀጽ 16(ለ) እና 17 ድንጋጌዎች እና ከይግባኝ መብት አንፃር መሰረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 34685 ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በጉዳዩ ላይ ሁለት የበታች ፍርድ ቤቶች ተመሳሳይ ውሳኔ የሰጡበት በመሆኑና የመጨረሻ ውሳኔ ያረፈበት በመሆኑ አመልካች ጉዳዩን ለማቅረብ የሚችሉት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ነው በማለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ተገቢውን ትእዛዝ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ